የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 7
ADDIS ABABA 25th December,2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፲/፪ሺ፩ ዓ.ም

የኤክሳይዝ ታክስ /ማሻሻያ/ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፫፻፹፫

CONTENTS

Proclamation No. 610/2008

Excise Tax (Amendment) Proclamation Page 4383

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፲/፪ሺ፩

## የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፫፻፯/፲፱፻፺፭ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና /፲፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኤክሳይዝ ታክስ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፲/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ማሻሻያ

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፫፻፯/፲፱፻፺፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፮/ ውስጥ "የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባሥልጣን" በሚል የተጠቀሰው ተሰርዞ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን" በሚለው ተተክቷል።

## PROCLAMATION NO. 610/2008.

## A PROCLAMATION TO AMEND THE EXCISE TAX PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Excise Tax Proclamation N0. 307/2002;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Excise Tax (Amendment) Proclamation No. 610/2008".

### 2. Amendment

The Excise Tax Proclamation No. 307/2002 is hereby amended as follows:

1/ The reference to the "Federal Inland Revenue Authority" in sub-article (6) of Article 2 of the Proclamation is repealed and replaced by the "Ethiopian Revenues and Customs Authority".

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ተተክቷል፤

“ለ. ታክሱን በሚገባ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሚሆነውን መረጃ የሚያሳይ መግለጫ ከግብር ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ቅጽ ላይ ሞልቶ በየ፴ ቀኑ ለግብር ባለሥልጣኑ በግንባር ቀርቦ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወክለው ሶስተኛ ወገን በኩል ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወዲያውኑ ገቢ ማድረግ አለበት።”

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፯ ተተክቷል፡-

“፲፯. <u>መቀጫን ስለማንሳት</u>

፩/ የግብር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚነሳው መቀጫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ መሠረት የሚታሰበውን ወለድ አይጨምርም።”

፬/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ውስጥ “የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ” ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ “ወይም ይግባኝ ካላቀረበ” የሚል ሐረግ ተጨምሯል።

፭/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ተጨምሯል፤

“፬ በግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለ በቂ ምክንያት ጉዳይን በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።”

2/ Sub-article (b) of Article 8 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub-article (b):

“b/ submit every 30 days, in a form which shall be supplied by the Authority, a declaration containing such information as may be necessary for proper collection of the tax and simultaneously pay the tax to the Tax Authority or through financial institution delegated by the Tax Authority or through electronic filing and payment system.”

3/ Article 17 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 17:

**“17. <u>Waiver of Penalty</u>**

1/ Administrative penalties may be waived in accordance with directives issued by the Tax Authority.

2/ The administrative penalties to be waived in accordance with sub-article (1) of this Article may not include the interest computed in accordance with Article 20 of this Proclamation.”

4/ The phrase “or appealed against its decision” is added before the phrase “within thirty (30) days” in sub-article (2) of Article 18 of the Proclamation.

5/ The following new sub-article (4) is added under Article 27 of the Proclamation:

“4/ The Tax Authority’s officer shall be held responsible for any damage caused to a tax payer delaying without any good cause, in the performance of his/her duty. Such employee in addition to being held liable for the damages, shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years”

## ፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of December, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**